??/? /??? 227023
?? 28/2/2015 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)
ቀነዓ ቂጣታ
ፈይሳ ወርቁ
ሰናይት አድነው
ደጀኔ አያንሳ

አመልካች - ወ/ሮ ሀሊማ ኡመር -- የቀረበ የለም
ተጠሪ - አቶ ሰይድ አህመድ -- ጠበቃ አብዮት አበበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ግንቦት 11 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 222530 ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 326 መሰረት መሆን ሲገባ የተጠሪ የይግባኝ ማስፈቀጃ ምክንያት ለይግባኝ ማስፈቀጃ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ በጠበቃ ስህተት የተፈጠረ መዘግየትን እንደበቂ ምክንያት ተወስዶ መፈቀዱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን የአሁን ተጠሪ አቶ ሰይድ አህመድ ባቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ከመልስ ሰጪ የአሁን አመልካች ጋር በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረን ክርክር ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 257669 መጋቢት 1 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የቅሬታ አቤቱታዬን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቤ በክርክር ላይ ቆይተን ሰበር ሰሚው ችሎት ክርክሩ ሂደቱን ያልጨረሰ ነው ሲል የዘገው በመሆኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሊያልፍብኝ ችሏል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈብኝ በኔ ምክንያት ባለመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ እንድችል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንድፈቀድልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ የአሁን ተጠሪም አመልካች በጠበቃ የሚከራከር በመሆኑና ህጉ በግልጽ ተቀምጦ እያለ ይግባኝ ለየትኛው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት እያወቀ ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ በጠበቃው ስህተት ለተፈጠረ መዘግየት፣ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት በቂ ባልሆነ ምክንያት በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥታለች፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራክሮ በመ/ቁጥር 222530 ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ጉዳዩን ለሰበር ሰሚው ችሎት አቅርቦ በቀጠሮ ቀይቶ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩ ሂደቱን ያልጨረሰ ነው ሲል መዝገቡን የዘጋው በመሆኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሊያልፍ ችሏል፡ አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት በበቂ በሆነ ምክንያት በመሆኑ በ10 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ያቅርብ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ የግራ ቀኙ ክርክር የሚፈታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 326(2) መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57360 ቅጽ 12 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ነው ወይስ አንድ ጉዳይ ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ከቀረበ ለይርጋ መቋረጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ የተሰጠ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተወስዶ ነው የሚለውን ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሐምሌ 11 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 326(1) አመልካቹ የቀረበለትን የፈቃድ መጠየቂያ አቤቱታ ተቀብሎ ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን ፍ/ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ይህንኑ በመዝገብ ላይ ካሰረፈ በኋላ የይግባኝ ማመልከቻውን በአስር ቀን ውስጥ አንዲያቀርብ ይፈቅድለታል ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ አመልካቹ በጊዜው ይግባኙን ማቅረብ ያልቻለው በቂ ምክንያት ስለመሆን አለመሆኑ የሚመዘነው በፍ/ቤቱ መሆኑን የመገልጽ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 326(2) በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለጸው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በአመልካቹ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ወይም ወኪሉ ያለመቅረብና በነዚሁ ጉድለት መሆኑ የታወቀ እንደሆነ ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ ቁጥር እንደተነገረው በቂ ምክንያት ነው ተብሎ ተቀባይነትን ለማግኘት አይችልም ሲል ይደነግጋል፡፡ አመልካቹ በጊዜው ይግባኙን ማቅረብ ያልቻለው ጠበቃዬ ወይም ነገረ ፈጁ ወይም ወኪሌ ስላልቀረበልኝ ነው በሚልና በነዚሁ ጉድለት ምክንያት እንደሆነ እንደበቂ መክንያት እንደማይወሰድ የሚገልጽ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 326(2) ጋር በተያይዘ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57360 ላይ የሰጠው ውሳኔ አመልካች በጠበቃው ስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት የይግባኝ መጠየቂያ ጊዜው ያለፈበት እንደሆነ እንደበቂ ምክንያት እንደማይወሰድ የሰጠው አስገደጅ የህግ ትርጉም ነው፡፡ አንድ ጠበቃ ለደንበኛው በሙያው በቅንነትና በታማኝነት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚገባው ግዴታ ሲሆን ጠበቃው በዚህ የጥብቅና አግልግሎት ውስጥ በያዘው ጉዳይ በፍጹም አይሳሳትም ተብሎም አይወሰድም፡፡ ጠበቃው ቢሳሳትም ፍ/ቤቱ ሥልጣኑ ባልሆነው ጉዳይ ተቀብሎ ክርክር ላይ ሊያቆየውም ባልተገባም ነበር፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች ጠበቃ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ግን ለተገቢው ፍ/ቤት የቀረበ ባለመሆኑ እና ይግባኙን የተቀበለው ፍ/ቤት ክርክር ላይ ያቆየው በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት እንደሆነ እንጂ በጠበቃው የስነ ምግባር ችግር ምክንያት የይግባኝ መጠየቂያው ጊዜ ያለፈበት ስለመሆኑ የሚያመለክት አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57360 ላይ

ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር ተመሳሳይነት ያለው አይደለም፡፡ በዚሁ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት በበቂ ምክንያት ነው ሲል ይግባኙን አንዲያቀርብ በመፍቀድ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ውሳኔ

1. የ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 222530 ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በ ዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የ ዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. መ ዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

አ/መ የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም